# እሳት… ከወለላዬ

እሳት

እሳቱን ከበፊት በወግ ሳያጠፉ
ፍሙን ምድር ቀብረው ሸፍነው እስካፉ
ዘመኑ ሲገፋ እድሜው ሲጠራቀም
ድንገት ነዶ ወቶ አጠፋ ሁሉንም
ከእሳቱ መካከል የወጣው ጦረኛ
ይበልጥ አቀጣጥሎ ተወው ለተረኛ
ይሄም አባብሶት አልጠፋም እሳቱ
ይሄው ሲንቦለቦል ሰላሳኛ አመቱ ::

ድርቅ

አቶ ድርቅ የሚሉት የጦርነት ወንድም
ብዙ ጥፋት ባገር አስከትሏል እሱም
እየተንኳተተ በየአስር አመቱ
ህዝብ አጭዶ ጨርሷል ተባብሮ ከሳቱ

በሽታ

ድህነት በርክቶ ረሀብ ሲበረታ
መንገድ ክፍት አግኝቶ አጥቅቷል በሽታ
ከሳቱ ጋር ሆኗል እሱም ተባባሪ
ሞትን ኡ ኡ ብሎ አስተኝቶ ተሪ

ሥራ አጥ

ቀየውን ሰው ለቆ በእሳቱ ሰበብ
እከተማ ማህል ገብቶ ሲረባረብ
የሚቆረጥመው የሚላስ የሚዋጥ
አጥቶ ተቀምጧል ተብሎ ስራ አጥ
ብዙ ተበድሏል በተለይ ወጣቱ
በሁሉም አቅጣጫ ለብልቦት እሳቱ

መሀይምነት

መሰረት የያዘ ስለሌለ ትምህርት
ህዝቡ አልተላቀቀም ከመሀይምነት
እንኳን ያልተማረ ፊደል ያላጠና
እሳቱ ምሁሩን አስቀርቷል መና

ጉቦ

ከሁሉም ከሁሉም ጊዜው የተመቸው
ስልጣንን ጨብጦ ለተቀመጠ ነው
ከሱም በታች ያለው ይኖራል ደልቦ
ኪሱን እየሞላ እያጨቀ ጉቦ

ጫት

ጫትንም ጨብጦ ያደረገው ወዳጅ
ይኖራል ባካልም በኑሮም ሳይደረጅ
አያድንም ብዙ ደብቆም አይደብቅ
ያቅታል በኋላ ከራስ ጋር መታረቅ
እሱም የሳት ልጅ ነው አዘናግቶ ገዳይ
እንኳን ሌላው ቀርቶ እራሱም አጎዳይ

ግድያ

ተንኮል ምቀኝነት ቅናትና ክፋት
ዝርፊያና ነጠቃ ማጅራት መቺነት
አስገድዶ መድፈር ሴተኛ አዳሪነት
መዋሸት ማጭበርበር የጎዳና ኑሮ
ባልባሌ ነገር ሰው መግደል አባሮ
የመጣ ነውና ከዚህ ገዳይ እሳት
እስቲ መላ ምቱ ፈጽሞ ለማጥፋት ::

<u>ወለላዬ</u>